# ቁርጥ ነው ዘንድሮ!!



ፍቅር በኔ ሰርጾ፣

ሕንጻውን አንጾ፣

ጮራውን ፈንጥቆ፣

ለኔ ሕይወት ሰጥቶ፣

ፋና ሆኖ በርቶ፣

ጉልቤቱ ጎልብቶ፣

ሰላሜ ተሟልቶ፣

ክብሬ ተወድሶ፣

በዓለም ዙሪያ ነግሶ፣

ገድሌ መነገሩ፣

ጠላት አሳብሮ፣

ቁርሾ በኔ ቋጥሮ፣

ሊወስዱ ሰላሜን፣

ባርያ አድርገው ሊጫኑኝ፣

ተስማምተው አበሩ፣

በኔ ተማከሩ።

ጨረቃ ፈንጥቃ፣

እንዲያ አብረቅርቃ፣

ልቤን ስትዘውረው፣

ቀልቤን ስትወስደው፣

መንፈሴን ስትሰርቀው፣

እኔን አስደምማ፣

ትዝታ አሸክማ፣

ይዛኝ የነጎደች፣

ጭልጥ ብላ የሄደች፣

በትዝታ አስጋልባ፣

ሰንደቅ አከናንባ፣

ወስዳ ስትመልሰኝ፣

ልቤን የረበሸኝ፣

ሰላሜን የነሳኝ፣

እኔን ያስቆዘመኝ፣

ፈተና የፈተነኝ፣

ሁሉ ተወግዶ፣

የነደደው በርዶ፣

ቀና ብዬ ብሄድ፣

ጉዞዬን ልራመድ፣




ማጎንበሴ ቀርቶ፣

ልቤ ተስፋ ሞልቶ፣

ሃሩርን ተክቶ፣

ግመቱን አብዝቶ፣

አየር አሳጥቶ ፣

ጋመኑን አብዝቶ፣

አንደበቴን ዘግቶ፣

አንከራቶ አቃቶ፣

አሳሬን ብበላ፣

እኔ እንዳልጉላላ፣

አዋሽ ብቅ ብሎ፣

በሜዳው ተንጣሎ፣

ደረስኩልህ ብሎ፣

ጢም ብሎ ሞልቶ፣

ኩልል ብሎ ታይቶ፣

ይዞኝ ሽፈተና፣

ሕይወት ሰጠኝና፣

መጥራቱ ቀረና፣

ውበቱን ቀይሮ፣

ምድሩን ቦርቡሮ፣

ጩሆቱን ጨምሮ፣

ደለሉን ከምሮ፣

ቧለተ ተንቧቸ፣

ውሃውን አንቧቸ፣

እንዲያ እያንቻረረ፣

አንጀቱ እያረረ፣

አምሮ መምጣቱ፣

መውጫ ማሳጣቱ፣

ዝምታው ትዕግስቱ፣

እርጋታው ውበቱ፣

ደፍርሶ ከመጣ፣

መውጫ የሚያሳጣ፣

ማዕበል ነው እሱ፣

ኋያል ነው አትርሱ፣

ገርድሶ ፈንድሶ፣

አውድሞ ደርምሶ፣

መንቅሮ አሽቀንጥሮ፣

ለማይሰማ ጆሮ፣

አድርጎ ድንቆሮ፣

ማለፉ አይቀርም፣

ብታምኑም ባታምኑም፣



ቁርጥ ነው ዘንድሮ፣

ቁርጥ ነው ዘንድሮ።

መይሳው ከምድረ ስዊድን

2014-04-17